ሰኔ 1 ቀን፣ 1997 ዓ.ም

# ግልጽ መግለጫ ለኢትዮጵያ ህዝብ

## ከልደቱ አያሌው (በግል)

አሁን የትግል እና የአካል እንቅስቃሴ በሌሎች ቁጥጥር ስር ውሏል ማለት ይቻላል። ምናልባትም ህይወቴ አደጋ ላይ የተቃረበ መሆኑን እያየሁ ነው። አላማዬ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ተፈጻሚ ሆኖ፣ አገራችን የዲሞክራሲያዊ ስርአት ባለቤት እንደምትሆን ግን ጥርጥር የለኝም።

ላለፉት አስራ ሶስት አመታት በትግል ላይ ስቆይ አንዱ እና ዋነኛው የትግል መርሆዬ ፍጹም ሰላማዊና ህጋዊ መሆን፣ ከፍርሃት ነጻ ሆኖ መገኘት ነው። በዚህ ምክንያት ምንግዜም በጸጥታ ሃይሎች መነጽር ውስጥ ያለሁ መሆኔን ባውቅም አንድም ቀን 'ማንም ከጀርባዬ ይከታተለኛል' ብዬ ተጨንቄ አላውቅም። በያዝኩት የፖለቲካ አመለካከት ምክንያት እስካሁን አምስት ጊዜ ታስሬ ተፈትቻለሁ።

ሁልጊዜም ከቤቴ ስወጣ ሌላ ስድስተኛ እስር ብቻ ሳይሆን፣ እስከሞት ለሚደርስ መስዋእትነት እራሴን አዘጋጅቼ ነው የምወጣው።

ይህንንም ትግል ውጤታማ ለማድረግ ከተፈለገ፣ "የትግሉን ውጤት ከራሴ የግል ጥቅም ጋር አያይዤ ማየት ለድል የማያበቃ እንደሆነ ስለምገነዘብ ግላዊነቴን አስሬዋለሁ፣ ገድዬዋለሁም። አስቀድሞ እንደታሰረና እንደሞተ በምቆጥረው ግላዊነቴ (ስጋዊነቴ) ውስጥ ግን መቼውንም የማይታሰርና የማይሞት፣ ግዙፍ እና ኃያል የህሊና ነጻነት ስላለኝ፣ ከስር አቱ የሚቃጣብኝን ተጽእኖ ሁሉ በትግሉ ውስጥ ያለኝን እንቅስቃሴ ገትቶት አያውቅም። ህዝቡ የሚያውቃቸውንና የማያውቃቸውን (ወደፊት ታሪክ የሚያወጣቸውን) በርካታ መከራዎችን ሁሉ ተጋፍጬ፣ እየወደቅኩና እየተነሳሁ እስከዛሬ ደርሻለሁ።

"ዛሬ" ልዩ ዛሬ ነው። የአገራችን የፖለቲካ ትግል ከጥቂቶች ተሳትፎ ወጥቶ ወደኋላ መመለስ በማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሶ፣ ትግሉ "የህዝብ ትግል" የሆነው ዛሬ ነው። ይህንን ሃቅ በውል መገንዘብ የተሳናቸው፣ ሁልጊዜ በራሳቸው የህልም አለም ውስጥ የሚኳዙት ገገሮቻችን ብቻ ናቸው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል፣ በዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ፣ በእኔ በኩል ብዙ ነፍሶች ኖረውኝ ደጋግሜ ብሞት እንኳ ሞቴ እንደሞት የሚቆጠር አይደለም። ትግሉን የህዝብ የማድረጉ ወሳኙ ድል ተገኝቷልና ከእንግዲህ ሞታችን የሚዘፈንለት እንጂ፣ የሚለቀስለት አይደለም።

ሆኖም ዛሬ ይህንን የግል መግለጫ ለመበተን የተገደድኩት፣ ያለሁበትን ወቅታዊ ሁኔታ እኔው ራሴ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሳወቅ እንዳለብኝ ስላመንኩና ይህንንም ለማድረግ አስገዳጅ ሁኔታ ስለተፈጠረብኝ ነው። በአሁኑ ወቅት ሰላማዊውን የትግል እንቅስቃሴ ለማድረግ በማልችልበት ሁኔታ ላይ እገኛለሁ።

ሰኞ - ግንቦት 29፣ 1997 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ከቅንጅቱ ምክር ቤት ስብሰባ ወጥቼ ወደስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ፓስፖርቴን ለማደስ ሄድኩ። ፓስፖርቴን ማደስ ያስፈለገኝ በመጪው ቅዳሜና እሁድ ስቶክሆልምና ለንደን ላይ የቅንጅቱ የገንዘብ ማሰባሰብ ፕሮግራም ስለሚካሄድ እዚያ ዝግጅት ላይ ሂጄ እንድካፈል፣ ቅንጅቱ ስለወሰነና ለዚህ ተልእኮ አርብ እለት ወደ ውጪ መሄድ ስለነበረብኝ ነው። ስደተኞች መስሪያ ቤት ቀርቤ ፓስፖርቴ እንዲታደስልኝ ስጠይቅ፣ ስማቸውን የማላውቀው ባለስልጣን ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ፓስፖርቴን መነጠቄን ነግረው አሰናበቱኝ።

ወደ ቢሮዬ ለመመለስ መኪና ውስጥ ስገባ ከሶስት በላይ የሆኑ የጸጥታ ሰራተኞች መኪናዎችና ከስድስት በላይ በሆኑ የጸጥታ ሰራተኞች መከበቤን ተገነዘብኩ።

ሁኔታውን ለስራ ባልደረቦቼ በስልክ ሪፖርት ለማድረግ ስሞክር ተንቀሳቃሽ ስልኬ

ከአገልግሎት ውጪ መደረጉን አወቅኩ።

ከዚያም ከላይ በጠቀስኳቸው ሰዎችና መኪኖች ታጅቤ ወደ ቢሮዬ መንዳት ቀጠልኩ። ነገር ግን 'ምናልባት የጸጥታ ሰራተኞች ማንም ሰው ሳያይና ሳያውቅ ሊያፍኑኝ አስበው ይሆናል' በሚል ስጋት ቢሮ የመሄድ ሃሳቤን ቀየርኩና በድንገት መንገድ ላይ ወደታየኝ አንድ ምግብ ቤት መኪናዬን አቁሜ ገባሁ። ማመን በማይቻል ፍጥነት አራት የጸጥታ ሰራተኞች ከፊት፣ ከጎንና ከኋላ አጅበውኝ ወደ ውስጥ ገቡ።

ሁኔታው ስላስገረመኝ ቆም ብዬ፤ "እኔን ፈልጋችሁ ነው?" ብዬ ጠየቅኳቸው።

"አንተን ሳይሆን ስራህን ነው የምንፈልገው" በማለት አንደኛው መለሰልኝ።

"ምሳዬን እስከምበላ ትታገሱኛላችሁ?" አልኳቸው።

"ትችላለህ" አሉኝና ለስላሳ መጠጥ አዝዘው በዙሪያዬ ተቀመጡ።

ምሳዬን እየበላሁ አንድ ሃሳብ መጣልኝ። 'ሰዎቹ ከምግብ ቤት ስወጣ ወደ እስር ቤት ሊወስዱኝ ወይም አደጋ ሊያደርሱብኝ ስለሚችሉ ብቻዬን እየነዳሁ መሄድ የለብኝም' ብዬ አሰብኩና ከምግብ ቤት አስተናጋጆቹ ውስጥ አንዱን፤ ቢሮዬ ድረስ አብሮኝ እንዲሄድ ጠየቅኩትና ፈቃደኛ ሆነልኝ።

ወደ መጸዳጃ ቤት እና እጅ መታጠቢያ ቤት ስሄድ የጸጥታ ሰራተኞቹ አልተለዩኝም። በዚያ ሁኔታ ከምግብ ቤቱ ወጥቼ በአራት መኪኖች ታጅቤ፤ ከቀኑ 7፡00 ላይ ጊዮን ፋርማሲ አጠገብ ከሚገኘው የኢዴአፓ_መድህን ቢሮ ደረስኩ።

እኔ ካለሁበት ቢሮ ፊት ለፊት በሚገኝ፤ የማን እንደሆነ በማላውቀው አንድ ቢሮ ውስጥ ሶስት የጸጥታ ሰራተኞች ገብተው በሩን ከፍተው ተቀመጡ። አንድ የጸጥታ ሰራተኛ ኮሪደር ላይ ሌሎች በርካታዎች ደግሞ ቢሮዬ ከሚገኝበት ህንጻ ስር ሆነው፤ የተጠናከረ ጥበቃ ማድረግ ጀመሩ።

በዚያው እለት እኔ ቢሮ ውስጥ ገብተው የወጡ አምስት የፓርቲያችን አባላት ከበር ላይ ተወስደው ታሰሩ። ሌሎች በርካታ ሰዎች ደግሞ መታወቂያ እየተጠየቁ ማስፈራሪያ ቃል እየተነገራቸው ለ አጭር ጊዜ እዚያው በር እንዲታገቱ ከተደረጉ በኋላ ተለቀቁ።

በዚህ ሁኔታ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ ቢሮዬ ከቆየሁ በኋላ፤ አቶ ኃይሉ ሻወልን ጨምሮ የቅንጅቱ አመራር አባሎች ቢሮዬ ድረስ መጥተው ወደ ቅንጅቱ ቢሮ ወሰዱኝ። ከነሱ ጋር ባደረግኩትም ጉዞ የአራቱ መኪኖች እጀባ አልተለየኝም።

ቅንጅቱ ቢሮ ከገባሁ በኋላ የተፈጠርውን ሁኔታ ለአንዳንድ የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች አስረድቼ፤ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት የቅንጅቱ አመራር በሆነ አንድ ወዳጄ መኪና ወደ ቤቴ አመራሁ። አሁንም ቤቴ እስከምደርስ ድረስ የአራቱ መኪና እጀባ አልተለየኝም።

ለሊቱንም ቤቴ በጸጥታ ሃይሎች ግልጽ ከበባ ስር ሆኖ አደረ። "ምናልባት ህዝብ ባላየበት ሁኔታ ለሊት ላይ ወደ እስር ቤት እወሰድ ይሆናል" ብዬ ተዘጋጅቼ ብጠብቅም የገመትኩት ሳይሆን ቀረ። ነገር ግን ከማለዳው 12፡00 ሰዓት ላይ ሬንጀር የለበሱ ወታሮችን የጫነና መሳሪያ የተጠመደበት አንድ ከባድ መኪና ግቢዬ መጥቶ ለጥቂት ጊዜ ከቆመ በኋላ ተመልሶ መሄዱን ቤተሰቦቼ ነገሩኝ።

<u>ማክሰኞ</u> - ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ አንድ የቅንጅቱ አመራር ቤቴ ድረስ መጥተው፤ ወደ ቅንጅቱ ቢሮ ወሰዱኝ። አሁንም ከመኖሪያ ቤቴ ጀምሮ ቅንጅቱ ቢሮ ድረስ በሶስት መኪኖች ታጅቤ ደረስኩ። የጸጥታ ሰራተኞቹ በመኪና አጅበውኝ በሂዱ ቁጥር ግን እጀባው የተረጋጋና ሰላማዊ አልነበረም። ብዙ መሰናክሎችና ማስፈራራቶች ያሉበት ጭምር ነው።

ቅንጅቱ ቢሮ ገብቼ ስለታሰሩት ሰዎች ሳጣራ ከእኔ ቢሮ ተወስደው የታሰሩ አምስት ሰዎች ማታ 2፡00 ሰዓት ላይ መለቀቃቸውን ተነገረኝ።

ታስረው ከነበሩት መካከል የደቡብ ቢሮ ተጠሪያችን የሆነውን አቶ ነፃነት ደመላሽን አግኝቼ ሳነጋግረው፤ እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ድረስ ለገሃር ጉምሩክ ግቢ ውስጥ በፖሊሶች ታስሮ እንዳመሸና በመጨረሻም "የአድማ ስራ ለመስራት ከልደቱ ጋር ለመሰብሰ እና መመሪያ ለመቀበል ነው የመጣኸው።" ብለው እንደጠየቁትና እሱም ለሌላ ተግባር የመጣ መሆኑን ካስረዳቸው በኋላ በማስጠንቀቂያ መለቀቁን ነገረኝ።

ማክሰኞ ሙሉ ቀን ቅንጅቱ ቢሮ ቅንጅቱ ቢሮ ዋልኩ። ምሳዬንም ከሌሎች ጓደኞቼ ጋር

እዚያው ቢሮ ድረስ መጥቶልኝ በላሁ። የጸጥታ ሰራተኞችም ከነመኪናቸው እዚያው ዋሉ። ማታ 12፡00 ሰዓት ላይ ስሄድም ተመሳሳዩ አጀብ ቀጠለ። እንዲያውም ወደ ቤት ደህና መግባቴን ለማረጋገጥ የተከተለኝን አንድ ሰው መንገድ ላይ አስቁመው በሽጉጥ አስፈራርተው እንዲመለስ አደረጉት።

ከፊቴ እየቀደመ በድንገት ፍሬን በመያዝ በጎን በኩል እየነዱ በማስፈራራት አጅበውኝ እና ለፊልም ስራ የወጣን በሚመስል ሁኔታ፣ ቤቴ አብሮን ሊያድር የወሰነ የትግል ጓደኛዬ ሆኜ ቤቴ ደረስኩ። እንደተለመደው በጸጥታ ሃይሎች ተከብቤ አደርኩና እንደገና ዛሬም ታጅቤ ቢሮዬ ገባሁ።

<u>ረቡዕ</u> - ቢሮዬ ሆኜ በከተማው የተፈጠረውን አሳሳቢ ችግር እየተከታተልኩ ባልሁበት ሰዓት ማንነቱን ከማላውቀው ሰው የስልክ ጥሪ ደረሰኝ።

በስልክ ያገኘኝ ሰው፣ ያለምንም የቅድሚያ ሰላምታ እና ንግግር፣ "ስማ ይህንን ሁሉ ሽብር አቀጣጥለህ እንደሁልጊዜ ታስረህ የምትፈታ እንዳይመስልህ። የቅንጅቱ አመራር ይህ ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ሲፈልግ በእምቢተኝነት ችግሩ ወደ እንደዚህ አይነት አመጽ እንዲያመራ ያደረግከው አንተ መሆንክን ደርሰንበታል። ስማ ይህ የተፈጠረ ብጥብጥና አመጽ እስከዛሬ ማታ መቆም ካልቻለ በአጭር ጊዜ በግልጽ አስፋልት ላይ ገድለን እንደምንጥልህ እወቅ" ብሎኝ ከእኔ ምንም አይነት ሳይጠብቅ ስልኩን ዘጋው።

ይህንን አባባል ሰኞ ጠዋት ቅንጅቱ ቢሮ ውስጥ ሆኜ አንድ የቅንጅቱ ከፍተኛ አመራር አንድ ታዋቂ ሚንስትር "ይህንን የተማሪዎች አመጽ ያስነሳው ልደቱ መሆኑን ደርሰንበታል።" ብሎ እንደነገረው የነገረኝን አስታወስኩና ተገረምኩ።

እኔ በቅንጅቱ ውስጥ ባለኝ የአመራርነት ተሳትፎ "ህዝቡ ከኛ የአመራር ቁጥጥር ወጥቶ ወደ ተናጠልና የማይፈለግ እንቅስቃሴ ውስጥ ከመግባቱ በፊት የህዝቡን ስሜትና ፍላጎት፣ ከጊዜና ከሁኔታዎች ጋር አገናዝበን ሰላማዊና ህጋዊ የአመራር ሚናችንን መወጣት አለብን" የሚል አስተሳሰብ ከመግለጽ በስተቀር በግሌ የተናጠል እርምጃ የመውሰድም ሆነ፣ የተለየ አቋም የማራመድ ፍላጎት ኖሮኝ አያውቅም። ያን የማድረግ አቅሙም የለኝም።

እንዲህ አይነት ችግር አገርቱ ውስጥ በተፈጠረ ቁጥር ለምን እኔ የተለየ ኢላማ እንደምሆን ግን እንቆቅልሽ ነው፣ አልገባኝም፡

በአሁኑ ወቅት አሁን ካለሁበት አንድ ደቂቃ ወደፊት በእኔ ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አላውቅም። በኔ በኩል ይህንን ያለሁበትን ሁኔታ ለምመካበት የኢትዮጵያ ህዝብ ከማሳወቅ በስተቀር ችግሩን ለማስወገድ ሌላ አቅምና እድል የለኝም። ማህበራዊ ግንኙነቴ ብቻ ሳይሆን፣ ለሰላማዊ ትግል የማደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከአቅሜ በላይ በሆነ አፈና ተገትቷል። እኔ ቢሮ ገብተው በሚወጡ ሰላማዊ ሰዎች ላይ በአሁኑ ሰአት የመሳሪያ ማስፈራራትና ድብደባ እየደረሰ መሆኑን በየደቂቃው እያየሁ ነው።

የድርጅታችን የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ሙሼ ሰሙ ጭምር ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እኔን አነጋግሮኝ ሲወጣ በር ላይ ተደብድቧል። ተንቀሳቃሽ ስልኬ ሳይቀር የሚሰራውና የማይሰራው በሌሎች ትእዛዝ ሆኗል።

አሁን ይህንን የግል መግለጫ በምጽፍበት ወቅት በከተማዋ የተለያዩ አቅጣጫዎች የተኩስ ድምጽ እየሰማሁ ነው። ብዙ ወጣቶች እንደሞቱና እንደቆሰሉ ከተለያዩ አካባቢዎች ስልክ እየተደወለ እየተነገረኝ ነው። ይህ አሳዛኝ ብጥብጥ ወደተረጋጋ ሁኔታ እንዲለወጥ ለማድረግ የሚያስችለኝ ከህዝብ ጋር የምገናኝበት መንገድ ባለመኖሩ በጣም አዝናለሁ። ለዚህ ሁሉ ብጥብጥ እና ችግር ተጠያቂው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

በአሁኑም ወቅት ከቢሮ እንዳልንቀሳቀስ ታግጃለሁ። "ከቢሮ እንዳትወጣ" ተብያለሁ፣ ያደርነውም በቢሮ ውስጥ ነው። ለሁሉም እኔ የሚመጣውን ሁሉ በደስታ እየጠበቅኩ ነው።

በመጨረሻም እኛ ኖርንም አልኖርንም የኢትዮጵያ ህዝብ ትግሉን ከዳር ለማድረስ ወደኋላ እንደማይል እተማመናለሁ።

አመሰግናለሁ።